በማቅረብ ቤቱን አመልካች እንዲያስተዳድርላቸውና በኪራይ ከሚሰበስበውም ገንዘብ ማካካሻው ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲከፍልላቸውና ውክልና ቢሰጡም ይሄው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ሳይሆን የሕብረት አምባ የመኖሪያ ቤት ኀ/ሥ/ማህበር እንደሆነና አመልካችም ቤቱን ለማኀበሩ እንዳስረከበ ቤቱም በባንክ ብድር ተሰርቶ የነበረ በመሆኑ ለባንክ መከፈል የነበረበትን ዕዳ አመልካች ከቤቱ የሰበሰበውን የኪራይ ገቢ በማኀበሩ ስም ለባንክ ስለመክፈሉ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲያደርግ አመልካች አቅርቧል፡፡ የቤት ቁጥር 545 የሆነው ቤት በፍርድ ጭምር የ1ኛ ተጠሪ አለመሆኑ ከተረጋገጠ የእራሳቸው ያልሆነን ቤት አመልካች በአደራ እንዲያስተዳድርላቸው በማስረከብ የኪራይ ማካካሻ በወኪሎቻቸው አማካይነት ያለአግባብ ሲቀበሉ እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ይህም አመልካች መክፈል የማይገባውን ክፍያ ሲፈጽም እንደነበር የሚያሳይ ሲሆን ሊከፍል የማይገባውን የከፈለ ደግሞ እንዲመለስለት መጠየቅ እንደሚችል በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2164 ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች ገንዘቡ ይመለስልኝ በማለት መጠየቅ አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስላለበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

**ው ሳ ኔ**

- አመልካች ክስ ያቀረበበት ብር 20,542.20 (ሃያ ሺህ አምስት መቶ አርባ ሁለት ከሃያ) በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
- ውሳኔው የተሻረ መሆኑ እንዲታወቅ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 22297

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት ተወካይ ቲጃኔ አባቡልጉ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ሸዋረገድ አባድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በወረዳው ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት በጠየቀው ዳኝነት መነሻ አድርጎ ያቀረበው ምክንያት እናቴ በካርታ ቁጥር 928 1392 ካሬ ሜትር በሆነው ቦታ ላይ የቤት ቁጥር 156 የሆነ ቤት አላቸው የእናቴ ወራሽ መሆኔን አረጋግጫለሁ ሆኖም ተከሣሽ የአሁን አመልካች ለሌላ ግለሰብ ስለሸጠብኝ ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚለውን ነው፡፡

አመልካችም ይህ በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበው ካርታ የተሰጠው በ1954 ዓ.ም. ነው፡፡ የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤትን ለመንግሥት ባደረገው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይህ ክስ የቀረበበት ንብረት የተወረሰ ነው፤ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የወረዳ ፍ/ቤትም በውርስ አግኝቼ የእራሴ ሆኗል በማለት ከሳሽ ይከራከር እንጂ ይህ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ንብረቱ በአዋጅ ቁጥር

47/67 የተወረሰ ስለሆነ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ውሣኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች ተወርሷል ይበል እንጂ ስለመወረሱ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ንብረቱ በከሳሽ በአሁን ተጠሪ ስም መሆኑን አልካደም የወራሽነት ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት መልስ ሰጭ የባለቤትነት ማስረጃ የለውም ማለቱ ተገቢ አይደለም ስለሆነም ካርታ እና ፕላን ያለውን ንብረት በሊዝ መሸጡ ተገቢ አይደለም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይኸው የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አመልካችን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል በማለት ነው፡፡

ግራ ቀኙም በዚህ ሰበር ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም ተጠሪ ሁከት ተፈጠረበት በተባለው ንብረት መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ለማሣየት መሠረት ያደረገው ወራሽ ነኝ በማለት ነው፡፡ ንብረቱም የአውራሽ የእናቴ ነው ለማለት ያበቃው በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበው ካርታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ካርታ በ1954 ዓ.ም. የተሰጠ ነው በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር ማስተባበያ አላቀረበበትም፡፡ ክዶም አልተከራከረም፡፡ አመልካች ይህ የንብረቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሲሆን ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ ግን ተወርሷል በማለት ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጎ ለቀረበው ክርክር ተጠሪ አልተወረሰም በማለት ተከራክሯል የቤቱ ካርታ የተሰጠበትን ጊዜ እና አዋጁ የወጣበትን ጊዜ እንደ መነሻ ፍሬ ነገር በመያዝ ንብረቱ የተወረሰ መሆኑን የግምት መነሻ በመስጠት አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህ ንብረት ያልተወረሰ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ የፍሬ



ነገር ክርክርም ሆነ ማስረጃ በማቅረብ አላረጋገጠም ይልቁንም በቃል በተደረገው ክርክር አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወጣ እኔ እስር ቤት ነበርኩኝ፤ የደርግ መንግሥት በአምባገነንነት በቀበሌ አማካኝነት ለሌሎች ሰዎች በኪራይ ሰጠብኝ የሚለውን መግለፁ ንብረቱ በእርግጥም የተወረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም ንብረቱ ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለውን ነጥብ በሚመለከት ማን ክርክሩን መጀመርና ማስረዳት እንዳለበት የሚያመለክተውን ድንጋጌ ባለመከተል እና ይህም ሥርዓት ቢዛነፍም እንኳ ከግራ ቀኙ ማን የተሻለ ማስረጃ አቅርቧል የሚለውን ነጥብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የፈፀመው ሁከት የለም ብለናል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22312 በሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ. 32640 በህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የወረዳው ፍ/ቤት በ/መ/ቁ 532/96 በጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 05349 በታህሣሥ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ